## መመሪያ ቁጥር 6/2012

## የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፤ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ኮሚቴ የወጣ መመሪያ

የኮቪድ-19 ስርጭት እየጨመረ በመምጣቱ ከሚኖረው የናሙና ቁጥር አንጻር የምርመራ ውጤቶችን በሰዓታት ውስጥ ማድረስ የማይቻል በመሆኑ በጤና ተቋማት ለሚከሰቱ ሞቶች ውጤት እስኪደርስ የአስክሬን ማስቀመጫ እጥረት ጫና በመፍጠሩ እንዲሁም ከጤና ተቋማት ውጪ ለሚከሰት ሞት ናሙና ከተወሰደ በኋላ የምርመራ ውጤት እስኪደርስ አስክሬን በቤት ውስጥ ማቆየት ለሟች ቤተሰብ እና ለአካባቢው ማህበረሰብ የስነ ልቦና እና ማህበራዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ እንዲሁም አስክሬን በቤት ወስጥ በሚቆይበት ጊዜ ቤተሰብን ለማፅናናት በሚል የሚፈጠረው የሰው መሰባሰብ ለበሽታው መተላለፍ እድል የሚፈጥር በመሆኑ ከዚህ በፊት ወጥቶ የነበረውን መመሪያ በማሻሻል በጤና ተቋምም ሆነ ከጤና ተቋም ውጪ ለሚከሰት ሞት አስከሬን በአፋጣኝ የሚቀበርበትን ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኮቪድ-19 ስርጭት በሀገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ በመሆኑ የመንግስት የህክምና ተቋማትና የህክምና ባለሙያዎች እየጨመረ በመጣው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በሚጠበቁ በተለይም ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ ለማድረግ በግል ቤት፣ በግል ህክምና ተቋማትና ሌሎች ቦታዎች የኮቪድ 19 የህክምና ክትትል የሚደረግበትን ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በአሁኑ ሰአት የአለም ሀገራት የአየር መንገዶቻቸውን ለአገልግሎት ክፍት እያደረጉ በመሆኑ ወደ ሀገራችን የሚመጡ መንገደኞች ከኮቪድ 19 ጋር በተያያዘ የሚስተናገዱበትን ስርአት መከለስና እና በድንበር አካባቢ የሚኖረውን የቁጥጥር ስርአት በግልፅ መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የሚኒስትሮች ኮሚቴ የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ አንቀፅ 7 መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፣

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. <u>አጭር ርእስ</u>

ይህ መመሪያ " **የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ኮሚቴ የወጣ መመሪያ ቁጥር 6/2012**" ተብሎ ሊጠራ ይችላል

2. <u>ትርጓሜ</u>

1. "አዋጅ" ማለት የኮቪድ 19 ሥርጭትን ለመከላከል ፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 03/2012 ነው፤
2. ደንብ ማለት የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል፣ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለዉን ጉዳት ለመቀነስ የወጣዉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012ን ለማስፈፀም የወጣዉ ደንብ ቁጥር 466/2012 ነዉ፤
3. በቂ የአየር ዝውውር ያለው ቦታ ማለት መኖሪያ ቤት ሆኖ በቂ የሚባል መስኮት ወይም አየር ማስገቢያ ያለው እና በላብራቶሪ ተመርምረው በበሽታው መያዛቸው የተረጋገጡ ሰዎች የሚኖሩበት ቤት ነው፤
4. ሞት ማለት በጤና ተቋም ወይም ከጤና ተቋም ዉጭ በማንኛውም ምክንያት የሚከሰት ሞት ነው፤ ቀላል የኮቪድ-19 ታካሚ ማለት በኮቪድ ኢንፌክሽን የተጠቃ ሆኖ የትኩሳት፣ የሳል ወይም ሌሎች ቀላል ምልክት ያለው ሆኖ የሳንባ ምች በሽታን ወይም ሌሎች የከፍተኛ ህመም ምልክቶች የማያሳዩ ታካሚዎች ናቸው፤
5. ምልክት የሌለው የኮቪድ-19 ታካሚ ማለት ምንም አይነት ምልክቶች የማያሳይ በኮቪድ-19 በሽታ የተጠረጠረ ወይም የተያዘ ሰው ነው፤
6. RT PCR ማለት በሞለኪዉላር ቴክኒክ የኮሮና ቫይረስ ልየታ ነው፤
7. RDT ማለት ፈጣን የ ኮቪድ 19 የምርመራ መሳሪያ ነው፤

8. IgM ማለት በቫይረሱ ተጠቅቶ የነበረ ሰዉ በሰዉነት ዉስጥ በተፈጥሮአዊ መንገድ የሚያመነጨቻዉ ከፕሮቲን የተሰሩ ጸረ-እንግዳ (አንቲበዲ) ሲሆን አንድ ሰዉ በቫይረሱ ከተጠቃ በሁዋላ በመጀመሪያ የሚመነጭ እና የቅርብ ጊዜ (7-10 ቀናት በፊት) ተጠቂ እንደነበር የሚያሳይ ነው፤

9. IgG ማለት በቫይረሱ ተጠቅቶ የነበረ ሰዉ በሰዉነት ዉስጥ በተፈጥሮአዊ መንገድ የሚያመነጨቻዉ ከፕሮቲን የተሰሩ ጸረ-እንግዳ (አንቲበዲ) ሲሆን ከሰስት ሳምንታት በፊት ተጠቂ የነበረ ሰዉ እንደበረ የሚያሳይ ነው፤

10. ፖዘቲቭ ማለት በምርመራ ቫይረሱ የተገኘበቻዉ ማለት ነው፤

11. ኔጌቲቭ ማለት በምርመራ ቫይረሱ ያልተገኘባቸዉ ማለት ነው፤

12. በአዋጁ እና በደንቡ ትርጉም የተሰጣቸዉ ቃላትና ሐረጎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁና ደንቦች ተፈፃሚ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ሞት በሚከሰትበት ጊዜ የሚኖር ቀብር፣ የአስከሬን ማጓጓዝ፣ የቀብርና የሀዘን ስርአትን በተመለከተ

**4. ከጤና ተቋማት ውጪ በተከሰተ ሞት በአስከሬን ማስተካከልና ግነዛ ወቅት የሟች ቤተሰብ ወይም ለሟች ሀላፊነት ያለበት ሰው የሚከተሉትን ግዴታዎች መወጣት ይኖርበታል፡-**

1) ከጤና ተቋማት ውጪ ሞት በተከሰተ ጊዜ ወዲያውኑ በአካባቢው ላለ የጤና ተቋም በማሳወቅ ከአስከሬኑ የኮቪድ-19 የላብራቶሪ ናሙና እንዲወሰድ የማድረግ፤
2) አስከሬን የሚያስተካክሉና የሚገንዙ ሰዎች የእጅ ጓንት፣የፊት ጭምብል ወይም ማስክ፣ ከፕላስቲክ የተሠራ ጋዋን ወይም ላስቲክ እንደ አስፈላጊነቱም ዓይን መከላከያ ወይም መነጽር እንዲለብሱ የማድረግ፤

3) አስክሬን የመገነዝ ሥራው በጥቂት ተጓዳኝ የጤና ችግሮች ወይም ህመሞች በሌሉባቸው፣ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርጉ በሚችሉ ሰዎች ብቻ እንዲከናወን የማድረግ፤

4) የሳልና ትኩሳት ምልክት ወይም ሌሎች የኮቪድ-19 ምልክት ያለባቸው ሰዎች አስክሬን ከሚያስተካክሉና ከሚገንዙ ሰዎች ጋር እንዳይሳተፉ የማድረግ፤

5) በአስከሬን ማስተካከልም ሆነ ግነዛ ሂደት ከሟች ቤተሰቦችም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖሩ ማንኛውም ግንኙነቶች ወይም በቦታው የሚደረግ እንቅስቃሴ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀትን በጠበቀ መልኩ፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ በማድረግ እንዲከናወን የማድረግ፤

6) አስከሬኑንም ሆነ አስከሬን ያለበትን ሳጥን ያለመነከካት ወይም ያለመሳም ግዴታ፤

7) አስክሬኑ በሳጥን ውስጥ ወይም በሌላ መጫኛ እቃ ከተደረገ በኋላ የሰውነት መከላከያ አልባሳት በመልበስ አስከሬን ያለበትን ሳጥን ወይም አስከሬን የተጫነበትን ሌላ እቃ፣ አስክሬኑም ሆነ ገናዦች የነካኳቸውን ሥፍራዎች ወይም ቁሳቁሶችን፣ሟች በታመመበት ወቅት ተኝቶ የነበረበት አልጋ፣ ሲገለገልባቸው ወይም በዙሪያ የነበሩ እቃዎች፣ የቤቱን ወለልና ሌሎች ከሟች ጋር ንክኪ የነበራቸውን እቃዎች በበረኪና ውሀድ እንዲፀዳ የማድረግ፣

8) ከአስክሬኑ የላብራቶሪ ምርመራ ከተወሰደ እና ከተገነዘ በኃላ በ 24 ሰዓት ውስጥ እንዲቀበር የማድረግ።

**5. ከጤና ተቋማት ውጪ በተከሰተ ሞት በአስከሬን ማስተካከልና ግነዛ ወቅት አስከሬን የሚያስተካክሉ የሚገንዙ፣ ሰዎች የሚከተሉትን ግዴታዎች መወጣት ይኖርባቸዋል፣**

1) ጓንት ለብሰው እየገነዙ በጓንታቸው ሌሎች የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ያለመነካካት ወይንም አስክሬኑን ከቦታ ቦታ ያለማንቀሳቀስና ያለመነካካት ግዴታ፤

2) የአስከሬን ማስተካከሉና መገነዝ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የተጠቀሙበትን ጓንት፣ የአፍና አፈንጫ መሸፈኛ እና ሰውነታቸውን የሸፈኑበትን ላስቲክ ወይም ጋዋን በአግባቡ የማስወገድ እና እጆቻቸውን በውሃ እና በሳሙና የመታጠብ ግዴታ፤

3) በአስከሬን ማስተካከልም ሆነ ግነዛ ሂደት ከሟች ቤተሰቦችም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀትን በጠበቀ መልኩና አፍኛ አፍንጫ መሸፈኛ በማድረግ ብቻ ማከናወን፤

**6. በአስከሬን ማስተካከልና ግነዛ ወቅት በለቅሶ ቦታ የተገኘ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ግዴታዎች መወጣት ይኖርበታል፣**

1) አስከሬኑንም ሆነ ሳጥኑን ወይም ሌላ አስከሬን መጫኛ እቃ ያለመነካካት፣ ያለመሳም እና የመሳሰሉትን ንክኪ ያለመፈጸም ግዴታ፤

2) አስከሬን አስተካካዮች ወይም ገናዦች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ስራው በተፋጠነ ሁኔታ እንዳይከናወን እንቅፋት ያለመሆን ግዴታ።

**7. በአስከሬን መጓጓዝ ወቅት የሚኖሩ ግዴታዎች**

1) አስከሬኑን ወደ ሚጓጓዝበት መኪና ወይም ሌላ የማጓጓዣ ዘዴ የመጫን ሀላፊነት ያለበት ሰው የአስከሬኑን ጭንቅላት ወደ ማጓጓዣው የፊተኛው ክፍል በማድረግ የመጫን ግዴታ አለበት፣

2) አስከሬኑን ወደ ማጓጓዣው የሚጭን ወይም ተሸክሞ ወደ ቀብር የሚወስድ ማናቸውም ሰው አፍና አፍንጫውን የመሸፈን እንዲሁም የእጅ ጓንት የማድረግ ግዴታ አለበት፤

3) አስከሬኑን የመጫን ወይም ማጓጓዝ ሀላፊነት ያለበት ማናቸውም ሰው አስከሬኑ ከተጫነ በኋላ፣ አስከሬኑ ቀብር ቦታ ከወረደ በኋላ እጁን በውሃና ሳሙና የመታጠብ ወይም በሳኒታይዘር የማፅዳት ግዴታ አለበት፤

4) አስከሬኑ በተሸከርካሪ የተጓዘ ከሆነ የተሸከርካሪው ባለቤት ወይም ሾፌሩ አስከሬኑ የቀብር ቦታ ከወረደ በኋላ ተሸከርካሪውን በበረኪና ውሀድ የማጠብ ግዴታ አለበት፤

5) ተሸከርካሪውን የሚያጸዳ ሰው አፍና አፍንጫውን የመሸፈንና የእጅ ጓንት የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሲሆን ከጨረሰ በኋላም እጁን በውሀና በሳሙና የመታጠብ ግዴታ አለበት፤

6) የሟች ቤተሰብ ወይም አስከሬኑን በተቻለ መጠን በሞተበት አካባቢ መቅበር ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም አስከሬን ለመቅበር ወደ ሌላ ቦታ ማጓጓዝ ግዴታ በሆነ ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ መጓጓዝ ይኖርበታል፣

7) ማንኛውም ሰው ቀብር ለማካሄድ ከቤት እስከ ስርአተ ቀብር ማስፈጸሚያ ቦታ የሚደረግ የአስክሬን መሸኘት ስርአት በእግር የሚደረግ ጉዞ የአፈና አፍንጫ መሸፈኛ በማድረግና ሁለት የአዋቂ እርምጃ በመራራቅ ከ50 ሰው ሳይበልጥ የማከናወን ግዴታ አለበት፣

## 8. በቀብር አፈፃጸም ወቅት የሚኖሩ ግዴታዎች

1) ማንኛውም በቀብር ላይ የሚገኝ የሟች ቤተሰብም ሆነ ሰው የቅርብ ቤተሰብን፣ የሃይማኖት ሥርዓት የሚያካሄዱ ሰዎችን፣ አስክሬን የመጫንና የማውረድ ስራ ሰዎችን እና የቀብር ጉድጓዱን የሚያዘጋጁ ሰዎችን ጨምሮ በአጠቃላይ ከ 50 በታች ብቻ ሆኖ የማከናወን ግዴታ አለበት፤

2) የሟች ቤተሰብ ወይም ለቀብሩ ሀላፊነት ያለበት ማንኛውም ሰው ቀብሩ የሟች ወይም የቤተሰብ ሃይማኖት በሚፈቅደው፣ በቅርበት በሚገኝ የቀብር ቦታ እንዲፈጸም ማድረግ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ ማድረግና ሁለት የአዋቂ እርምጃ ተራርቆ የመፈጸም ግዴታ አለበት፣

3) ማንኛውም የቀብር ስርአት የሚፈፅም ሰው አስክሬን ያለበትን ሳጥን ወይም አስክሬን የተሸፈነበትን እቃ በቀብር ሥፍራ ያለመክፈት ግዴታ አለበት፣

4) ማንኛውም በቀብር ቦታ የተገኘ ሰው የአስክሬኑን ሳጥን ወይም አስከሬኑ የተጫነበትን ወይም የተሸፈነበት እቃ ያለመንካት ወይም በመሳም ያለመሰናበት ግዴታ አለበት፣

5) ግብዐተ መሬት የሚፈጽሙ ሰዎች ግብአተ መሬቱን እንዳጠናቀቁ እጃቸውን በውሀ እና በሳሙና በአግባቡ የመታጠብ ግዴታ አለባቸው፣

6) አስክሬን የተጓጓዘባቸው ተመላሽ የሚሆኑ እንደ አልጋ ወይም ቃሬዛ ካሉ እነዚህን እቃዎች የመመለስ ሀላፊነት ያለበት ሰው አንድ እጅ በረኪና በዘጠኝ እጅ ውሀ በተዘጋጀ ውህድ በአግባቡ የማፅዳት ወይም እንዲፀዱ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

7) ማንኛውም ሰው በአስክሬን ማጓጓዝ ወይም በግብአተ መሬት ወቅት የተጠቀሙባቸውን ጓንቶች በአግባቡ ማውለቅና ክዳን ባለው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ የመጣል ወይም መጣያ በቅርበት ካልተገኘ የማቃጠል ግዴታ አለበት፤

8) ማንኛውም በቀብር ቦታ ላይ የተገኘ ሰው ስርዐቱ ሲጠናቀቅ እጁን በውሀ እና በሳሙና መታጠብ ወይም በእጅ ማጽጃ ሳኒታይዘር የማፅዳት ግዴታ አለበት።

## 9. ከቀብር ስነ-ስርአት በኋላ የሚኖሩ ግዴታዎች

1) ከቀብር በኋላ ለቅሶ መቀመጥ በድንኳን፣ በቤት ውስጥ ወይም ለዚሁ በተዘጋጀ ቦታ ላይ ሲደረግ ሀዘንተኛው እና የቤተሰቡ አባላት እና ለቅሶ የሚደርሰው ሰው ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀትን በመጠበቅ፣ የአፍ መሸፈኛ ማስክ በማድረግ እና ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መከናወን አለበት።

2) በድንኳን፣ በቤት ውስጥ ወይም ለለቅሶ በተዘጋጀው ቦታ የተቀመጠ ሀዘንተኛ ፣ ቤተሰቡ እና ለቅሶ የሚደርሰው ሰው ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት የመጠበቅ፣ የፊትና የአፍንጫ መሸፈኛ ማድረግና በማናቸውም ምክንያት ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለመነካካት ግዴታ አለበት።

3) በለቅሶ እና በቀብር ስርአት ወቅት ከሌሎች ሰዎች ጋር በመነካካት ወይም ሊያነካካ በሚችል መልኩ መመገብ፣ ወይም በለሌሎች ሰዎች በተነካኩና ባልታጠቡ እቃዎች መመገብ የተከለከለ ነው ፤

4) ማንኛውም ለቅሶ ሊደርስ የመጣ ሰው ወደ ለቅሶ ቤት ከመግባቱ በፊትና ከለቅሶ ቤት ሲወጣ እጁን በውሀና ሳሙና የመታጠብ ወይም በሳኒታይዘር የማፅዳት ግዴታ አለበት፣

5) ሌሎች ከሀይማኖታው ተቋማት ውጪ የሚከናወኑ የሀዘን ስርአቶች እንደ ሰባት፣ አርባ ፣ ሙት አመትና ሰደቃ የመሳሰሉትን ለማክበር አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ መገኘት የተከለከለ ነው።

6) በዚህ አንቀጽ የተቀመጡትን የተከለከሉ ተግባራት ለቅሰው የሚመለከተው እድር ሀላፊ ወይም የሚወክለው አባል ወይም በአካባቢው የሚገኝ ፖሊስ ወይም ሚኒሻ ተቋም በአግባቡ የማስፈጸም የመከታተል እና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት።



Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

7) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ  የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እድር የሌለው ሀዘንተኛ በአካባቢው ለሚገኝ የፖሊስ ወይም የሚኒሻ ተቋም  ማመልከት አለበት፤ በአካባቢው የሚገኝ የፖሊስ ወይም ሚኒሻ ተቋም  የቀብር እና የለቅሶ ስርአቱን በአግባቡ መፈጸሙን የሚከታተል እና የሚቆጣጠር አባል መመደብ አለበት።

8) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 እና 7 የተመለከቱት አካላት ሀላፊነታቸውን ካልተወጡ በህግ አግባብ ተጠያቂ ይሆናሉ።

## 10. የእምነት ተቋማት  ሀላፊዎችና የሀይማኖት አባቶች   ግዴታዎች

1) የእምነት ተቋማት ሀላፊዎች አስከሬኑ ወደ ቀብር ሥፍራ ከመምጣቱ በፊት  ከሟቹ ላይ የምርመራ ናሙና መወሰዱን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፣

2) የእምነት ተቋማት ሀላፊዎች በሥርዓተ ቀብር ላይ የሚገኙ የሰው ቁጥር የሀይማት አባቶችን ጨምሮ ከ50 አለመብለጡን የመከታተል ግዴታ አለባቸው፤

3) በሥርዓተ ቀብር ላይ  የሚገኙት የሀይማት ተቋማት ሀላፊዎች ወይም የሀይማት አባቶች አፍና አፍንጫቸውን የመሸፈን እና ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፤

4) በለቅሶ ስርአቱ ላይ ለሚገኘው ማህበረሰብ  ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ በየጊዜው በመንግስት የሚወጡትን መመሪያዎች የመከታተልና ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው የማስተማር ግዴታ

## 11.የጤና  ሚኒስቴር፣ የጤና ቢሮዎችና በፌዴራልና በክልሎች በየደረጃው ያሉ የመንግስት የጤና ተቋማት ወይም  ጽህፈት ቤቶች ግዴታ

1) ማህበረሰቡ የዚህን መመሪያ ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲያውቅ የማስተማር ግዴታ

2) ለእድር አመራሮች እና አስከሬን ለሚገንዙ ሰዎች ስልጠና የመስጠት ግዴታ

3) በመኖሪያ ቤት ውስጥ ሞት ሲኖር በወቅቱ መረጃ ማግኘት እና ናሙና በአስቸኳይ ሊወሰድ የሚቻልበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣ ተፈጻሚነቱንም መከታተል እና ማረጋገጥ፤

4) የአስክሬን አያያዝ፣ የማጓጓዝ፣ የሥርዓተ ቀብር እንዲሁም በቤት ውስጥ ሊኖር የሚችለው የሀዘን ሥነ-ሥርዓት ዙሪያ ለህብረተሰቡ እና ለባለ ድርሻ አካላት ሙያዊ እገዛ ማድረግ

## 12.በፌዴራልና ክልሎች በየደረጃው የሚገኝ ፖሊስ ተቋማት ግዴታ

1) የቀብር ሥነ-ስርዓት እና የሀዘንተኞች አቀማመጥ በዚህ መመሪያ መሰረት እንዲከናወን የማድረግ፣
2) ቤተሰብ የሌለው ሰው ሞት ሲከሰት ወይም አስክሬን ሲገኝ አስፈላጊውን የብክለት መከላከል ጥንቃቄዎች ተከትሎ ወደ ጤና ተቋም በማጓጓዝ ምርመራ እንዲደረግ እና የቀብሩ ሥርዓት በአግባቡ እንዲካሄድ ተገቢውን ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ
3) የወንጀል ምርመራ የሚጠይቅ ሞት ሲከሰት ወይም አስክሬን ሲገኝ አስፈላጊውን የብክለት መከላከል ጥንቃቄዎች ተከትሎ ወደ ጤና ተቋም በማጓጓዝ ምርመራ እንዲደረግ እና የቀብሩ ሥርዓት በአግባቡ እንዲካሄድ ተገቢውን ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ።

## 13.የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ግዴታ

የሟች ቤተሰቦች የስነ-ልቦና ድጋፍና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ያስተባብራል፣

## 14.በፌዴራልና በክልሎች የሚገኙ የዞን፣ የከተማ፣ ወይም የወረዳ አስተዳደር ግዴታ

የአስክሬን አያያዝ፣ የማጓጓዝ፣ የሥርዓተ ቀብር እንዲሁም በቤት ውስጥ ሊኖር የሚችለው የሀዘን ሥነ-ሥርዓት በዚህ መመሪያ መሠረት የማስፈጸም ግዴታ አለባቸው፣

## 15.የገጠር ቀበሌዎች ወይም የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ግዴታ

1) የቀበሌዉ አስተዳደር የቀብር ስነ-ሥርዓቱን የማስፈፀም ግዴታ አለበት፣
2) የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በአስክሬን አያያዝ፣ የቀብር አፈጻጸም እና በሐዘን ስነስርአት አፈፃፀም ወቅት መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች ለአድር አመራሮች እና ማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

**16.በጤና ተቋማት ወይም በኮቪድ 19 የህክምና ማእከላት ሞት በተከሰተ ጊዜ የጤና ተቋማቱ ወይም የኮቪድ 19 ህክምና ማእከላት ግዴታ**

1) ሞት የተከሰተባቸው ማእከላት አስከሬን ለቤተሰብ ከመስጠታው በፊት የኮቪድ-19 ምርመራ ለማድረግ ናሙና የመውሰድ እና ስለመወሰዱ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ፣
2) መረጃውን በየጊዜው ለጤና ሚኒስቴር ወይም ለጤና ቢሮ ወይም ለህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የማሳወቅ፣
3) አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ አስከሬን በማስተካከልና በመገነዝ ለሟች ቤተሰብ ፣ ሟች ቤተሰብ የሌለው ከሆነ ለፖሊስ ወይም ለአካባው መስተዳድር ወይም መዘጋጃ ቤቶችአስከሬኑን የማስረከብ፣
4) አስከሬኑን በማጓጓዝና በቀብር ስነ-ስርአት ወቅት ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች ለሟች ቤተሰብና ማህበረሰቡ የማስተማር፣

**17.በጤና ተቋማት ወይም በኮቪድ 19 ህክምና ማእከላት የሞተ ሰው ቤተሰቦች የሚከተሉትን ሀለፊነቶች የመወጣት ግዴታ አለባቸው፣**

1) የሟች ቤተሰቦች የአስከሬን ማጓጓዣ በማቅረብና አስፈላጊውን የብክለት መከላከያ ጥንቃቄ በማድረግ የአስከሬን ማጓጓዝና የቀብር ስነ-ስርአቱን በራሳቸው በተዘጋጀ ቦታ የማስፈፀም ግዴታ አለባቸው፣
2) አስከሬን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ቤት ሳይወስዱ በቀጥታ ወደ ቀብር ቦታ የመውሰድ ግዴታ፣
3) በአስከሬን ማስተካከልና መገነዝ፣ ማጓጓዝ፣ ቀብር አፈፃጸም ወይም የሀዘን ስነ-ስርአት በሚያከናውኑበት ጊዜ በዚህ መመሪያ ከጤና ተቋማት ውጪ ለሚከሰት ሞት የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን በሙሉ ተግባራዊ የማድረግ፣
4) በተቻለ መጠን ሞት በተከሰተበት አካባቢ የቀብር ስነ-ስርአቱን የመፈፀም ወይም አስከሬኑን ወደ ሌላ ቦታ ማጓጓዝ ግዴታ በሆነ ጊዜ በከፍተኛ ጥንቃቄ ማጓጓዝ፣

**18.በጤና ተቋማት ወይም በኮቪድ 19 ህክምና ማእከላት ሞት በሚከሰትበት ጊዜ የፖሊስ ወይም የሚኒሻ ግዴታ**

1) .የቀብር ሥነ-ስርዓት እና የሀዘን አቀማመጥ የጥንቃቄ መመሪያዎች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በወጣው መመሪያ መሰረት እንዲተደገብሩ የማድረግ ግዴታ፣
2) ቤተሰብ የሌለው ሰው ሞት ሲከሰት የቀብሩ ሥርዓት በአግባቡ እንዲካሄድ ተገቢውን ድጋፍ እና ክትትል የማድረግ፣

**19.የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ግዴታ**

የሟች ቤተሰቦች የስነ-ልቦና ድጋፍና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ያስተባብራል፣

**20.ብሔራዊ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

1) ቤተሰብ የሌለው ሰው በጤና ተቋማት በሚሞትበት ጊዜ ቀብር የሚያስፈፅም ብሔራዊ የቀብር ሥነ ስርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተቋሙሟል፤
2) አስተባባሪ ኮሚቴው በሰላም ሚኒስቴር ሰብሳቢነት ይመራል፤
3) የኮሚቴዉ አባላት የስራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፣የኢሚግሬሽንና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ፣ እንደአግባብነቱ የህግ አስከባሪ አካላት እንዲሁም ሌሎች በሚኒስትሮች ኮሚቴ የሚመረጡ አካላት ይሆናሉ፤
4) ክልሎችና ከተማ አስተዳደርች በተመሳሳይ ሁኔታ በየደረጃው የቀብር ሥነ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ማቋቋም አለባቸው፤
5) ቤተሰብ የሌለው ሰው በጤና ተቋማት በሚሞትበት ጊዜ ለቀብር የሚሆን በጀት መመደቡን የማረጋገጥ ሃላፊነት የብሔራዊ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ እና በክልል እና ከተማ አስተዳደሮች የሚቋቋሙ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

**21.የጤና ሚኒስቴር፣ የጤና ቢሮዎችና በፌዴራልና በክልሎች በየደረጃው ያሉ የመንግስት የጤና ተቋማት፣ ጽህፈት ቤቶች ወይም ኮቪድ 19 ህክምና ማእከላት ግዴታ**

1) በጤና ተቋማት ወይም ኮቪድ 19 ህክምና ማእከላትሞት በሚከሰትበት ወቅት አስከሬኑን ገንዘው ለሟች ቤተሰቦች ወይም ሟች ቤተሰብ የሌለው እንደሆነ ለፖሊስ፣ ለአካባቢው መስተዳድር ወይም ለመዘጋጃ ቤቶች ያስረክባሉ፣
2) የአስከሬን ማሸጊያ ፕላሲትክ ያዘጋጃሉ፤
3) የአስከሬን ማቆየት ሲያስፈልግ አስከሬን ያቆያል፤
4) በአስከሬን አያያዝ፣ በአስከሬን ማጓጓዝ፣ የቀብር ስነ-ስርዓት ወይም የሀዘን ስነ-ስርአት በሚፈጸምበት ወቅት መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች የማህብረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል፤

**22.የኢሚግሬሽንና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ኃላፊነት**

1) በመላው ሀገሪቱ በኮሮና ምክንያት በጤና ተቋማትና ከጤና ተቋማት ውጪ የሚከሰቱ ሞቶችን ይመዘግባል ፤መረጃ ያደራጃል፤
2) በኮሮናና ተያያዥ ጉዳዮች በሚከሰቱ ሞቶች ምክንያት የውርስና የመሳሰሉ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ለሚከሰቱ ማህበራዊ ቀውስ ለመከላከል የሚረዳ መረጃ ያደራጃል።

**23.በፌዴራል ከተማ አስተዳደሮች፣ በየክልሉና ከተማ አስተዳደር የሚገኙ መዘጋጃ ቤቶች፣ የወረዳዎችና ቀበሌዎች መዋቅሮች ቤተሰብ የሌለው ሰው በሚሞትበት ጊዜ የሚኖራቸው ተግባርና ኃላፊነት**

1) ለሁሉም ሀይማኖቶች የቀብር ቦታዎችን ያዘጋጃል፤
2) ለቀብር ስነ-ስርዓት የሚውል በጀት ይመድባል፣
3) የአስከሬን አያያዝ፣ ትራንስፖረት እና የቀብር ስነ-ስርዓት ላይ መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች የማህብረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል፤

4) የሀይማት ተቋማትና እንደ እድሮች ያሉ የማህበረሰብ መረዳጃና በጎ አድራጎት አደረጃጀቶችን በማስተባበር የሟች ቤተሰቦች የስነ-ልቦና ድጋፍ እና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ያስተባብራል፤

5) በማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰት ሞትን ቅኝት ያደርጋል፣ በዚህ መመሪያ መሰረት የቀብር ስነ-ስርዓት እንዲፈፀም ያደርጋል።

6) ከጤና ተቋማት ቤተሰብ የሌላቸውን አስከሬን በሃላፊነት ተረክበው የመውሰድ እና የቀብር ስነ ስርአት የማስፈፀም ግደታ።

**24.የሌሎች ተቋማት ሀላፊነት**

በዚህ መመሪያ ከጤና ተቋማት ውጪ ለሚከሰት ሞት ሀላፊነት የተሰጣቸው አካላት እንደአግባብነቱ በጤና ተቋማት ወይም ኮቪድ 19 ህክምና ማእከላት ለሚከሰት ሞትም ተፈፃሚ ይሆናል።

# ክፍል ሶስት

# በኮቪድ-19 በሽታ የተጠረጠረ ወይም የተያዘ ሰው ማድረግ ስላለበት ጥንቃቄ፣ በቤት ውስጥ፣ በዩኒቨርሲቲ ወይም ተለይቶ በተዘጋጀ ተቋም ውስጥ ወይም በተፈቀደላቸው የግል ህክምና ተቋማት የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ስለሚያስችሉ መስፈርቶች

**25. በኮቪድ-19 በሽታ የተጠረጠረ ወይም በበሽታው በተያዙ ሰው የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ሊያደርግ ይገባዋል**

1) በቤተሰብ ወይም በራሱ ተለይቶ በተዘጋጀ በቂ የአየር ዝውውር ያለው (በርና መስኮት) ባለው ክፍል ውስጥ መቆየት፣

2) በቂ የሚባል የአየር ዝውውር በማይኖርበት ጊዜ ከሌላው የቤተሰብ አባላት በ 2 ሜትር ርቀት መጠበቅ እዲሁም የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል መጠቀም፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
Democratic Republic ... Federal Attorney ...

3) ራስን ቢያንስ ለ 14 ተከታታይ ቀናት ማግለል

4) የኮቪድ-19 በሽታ ምልክቶቹ ከተባባሱ ወዲያውኑ ለሚመለከተው ተቋም በስልክ ሪፖርት ማድረግ፣

5) በሚያስሉበት እና በሚያስነጥሱበት ወቅት አፍ እና አፍንጫን በተገቢው መንገድ መሸፈን፣ የተጠቀሙበትን ሶፍት፣ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ፣ የእጅ ጓንትና መሰል ቁሳቁሶችን ክዳን ባለው ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ወይም በፕላስቲክ ከረጢት ቋጥሮ በጥንቃቄ መጣል፣

6) ማንኛውም ንክኪ በሚኖሩበት ሰዓት በውሃና ሳሙና ወይም በአልኮል በተዘጋጀ የዕጅ ማጽጃ የእጅ ንፅህናን መጠበቅ

7) ከቤተሰብም ሆነ ማናቸውም ሰው ጋር ያለን አላስፈላጊ ቅርርብ ማስወገድ ወይም ማህበራዊ ወይም አካላዊ እርቀትትን መጠበቅ

8) ሰዎች በጋራ ከሚጠቀሙባቸው እንደ ሳሎን፣ መታጠቢያ እና ምግብ ማብሰያ ያሉ በታዎች ከመጋራት መቆጠብ ወይም መቀነስ፤

9) የተለያዩ የመጠቀሚያ እቃዎችን፣ በሮችን እና የመሳሰሉትን ነገሮች ከመንካት መቆጠጠብ፣ እነዚህን እቃዎች ነክቶ ከሆነም ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት በአግባቡ እንዲጸዱ የማድረግ

10) ከተቻለ ሌሎች የማይጠቀሙባቸውን መጸዳጃ ቤቶች፣ ማእድ ቤቶችና ሌሎች መገልገያ እቃዎችን የመጠቀም፣ ካልሆነ ከተገለገሉ በኋላ በሳሙና እና በውሃ ማፅዳት፣

## 26.በቤት ውስጥ የኮቪድ-19 በሽታ ህክምና አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶች

የሚከተሉትን ሁሉንም መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በቤት ወስጥ የኮቪድ 19- ህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል፣

1) በቤቱ ሆኖ የኮቪድ-19 ህክምና ለማግኘት ፍቃደኛ የሆነ፣
2) ቀላል ወይም ምንም አይነት የኮቪድ-19 ምልክት የሌለበት፣
3) በቤት ውስጥ የቆይታ ጊዜ አጋዥ ወይም ረዳት ያለው እንዲሁም እራሱን መርዳት የሚችል
4) የምግብ እና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማግኘት ወይም ማሟላት የሚችል፣
5) በተመሳሳይ ቤት ውስጥ የሚኖር ሌላ ሰው የግል ንፅህና መጠበቂያዎችን እንዲሁም የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭብሎችን ማግኘት የሚችል እንደሆነ

6) የኮቪድ-19 የተገኘበት ሰው ከሌሎች ተጓዳኝ በሽታዎች ማለትም የልብና የደም ቧንቧ በሽታ ፣ የስኳር በሽታ ፤ አስም፣ ኤች አይቪ፣ ቲቢ ፣ ካንሰርና የመሳሰሉት በሽታዎች ካሉባቸው ሰዎች ጋር አብሮ የማይኖር ከሆነ፣

7) የኮቪድ-19 የተገኘበት ሰው ከቤት ላለመውጣት ወይም ማናቸውም ጠያቂ ወደ ቤት እንዳይመጣ ለማድረግ ማረጋገጫ የሚሰጥ ከሆነ፣

8) እራሱን ከሌሎች የቤተሰብ አባላት ለይቶ ማቆየት የሚያስችል ክፍል ወይም ከቤተሰብ አባላት በ 2 ሜትር ርቀት ላይ መቆየት የሚያስችል ክፍል ያለው እንደሆነ

9) በጤና ቡድን በቋሚነት ለመደገፍ ፈቃደኛ የሆነ፣

## 27.ከህክምና አገልግሎት መስጫ ውጭ በልዩ ሁኔታ በተዘጋጁ ተቋማት (በዩኒቨርሲቲዎች፣ በት/ቤቶች፣ በወጣትና የስፖርት ማእከላት እና የመሳሰሉት) ውስጥ የኮቪድ-19 በሽታ ህክምና አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶች

የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ከህክምና አገልግሎት መስጫ ውጭ በልዩ ሁኔታ በተዘጋጁ ተቋማትውስጥ የኮቪድ 19 ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡-

1) በለሙያዎች የሚጠየቁትን የቤት ውስጥ ለይቶ ማቆያ መስፈርቶችን ማሟላት የማይችል፣

2) ቀላል ወይም ምንም አይነት የኮቪድ-19 ምልክት የሌለበት፣

3) በቤት ውስጥ የቆይታ ጊዜ አጋዥ ወይም ረዳት የሌለው ወይም እራሱን በቀላሉ መርዳት የማይችሉ

4) የምግብ እና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን በቀላሉ ማግኘት የማይችል፣

5) በሚኖርበት ቤት ውስጥ ህክምናውን ቢከታተሉ አብሯቸው የሚኖሩ ሰዎችን ለበሽታው በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ ከሆነ፣

## 28.በተፈቀደላቸው የግል የህክምና መስጫ ተቋማት ውስጥ የኮቪድ-19 ህክምና አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶች

የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሰዎች በተፈቀደላቸው የግል ህክምና መስጫ ተቋማት ውስጥ የኮቪድ 19 ህክምና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፣

1) በግል የኮቪድ 19 ህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ ተኝቶ ለመታከም ፍቃደኛ የሆነ፣

2) በግል የኮቪድ 19 የህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ ከፍሎ የመታከም አቅም ያለው፣

3) ቀላል፣ ወይም ምንም አይነት የኮቪድ-19 ምልክት የሌለባቸው ሆነው፤ በሚኖሩበት ቤት ውስጥ ህክምናውን ቢከታተሉ አብሯቸው የሚኖሩ ሰዎችን ለበሽታው በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉ ከሆነ፣

4) የጤና ሚኒስቴር ስለየግል የኮቪድ 19 ህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ዝርዝር ማንዋል ያዘጋጃል፡፡

# ክፍል አራት

## የኳራንቲን እና የድንበር ላይ ጤና ቁጥጥርን በተመለከተ

**29.በቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል የኮሮና ቫይረስ የRT PCR ምርመራ ውጤት ይዞ የሚመጣ መንገደኛን በተመለከተ**

1) በቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል የሚገባ ማንኛውም ተጓዥ ከመጣበት ሀገር ከ 72 ሰዓት በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ የRT PCR ምርመራ ኔጌቲቭ ውጤት ይዞ ከመጣ በአየር መንገዱ የጤና ምርመራ ዴስክ የሙቀት እና የኮቪድ-19 ምልክቶች ልየታ ተደርጎ ናሙና ከተወሰደ በኋላ አድራሻው ተመዝግቦ ለ14 ቀናት በቤቱ ራሱን ለይቶ የመቆየት ግዴታ አለበት፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የላቦራቶሪ ምርመራ የተደረገለት ሰው ውጤት ፖዚቲቭ ከሆነ በአድራሻው ተፈልጎ በተቀመጠው የኮቪድ-19 ህክምና መመሪያ መሰረት ህክምና እና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፣

3) መንገደኛው ከአዲስ አበባ ውጭ ከሄደና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የላቦራቶሪ ምርመራው ውጤት ፖዘቲቭ ከሆነ ለሚገኝበት የክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ በማሳወቅ ህክምና እና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

4) በቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል የሚገባ ማንኛውም ተጓዥ የኮቪድ-19 ምልክት የሚያሳይ ከሆነ ውጤቱ እስሚደርስ መንግስት ባዘጋጀው ለይቶ ማቆያ የመግባት ግዴታ አለበት፤

5) የኮሮና ቫይረስ ፖዚቲቭ ውጤት ይዞ በአየር መንገድ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

## 30.በቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል የኮሮና ቫይረስ PRT PCR ምርመራ ውጤት ሳይዝ የሚመጣ መንገደኛን በተመለከተ

1) በቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ የሚገባ መንገደኛ ከሚመጣበት ሐገር ከ72 ሰዓት በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ PRT PCR ምርመራ ሰርትፊኬት ይዞ ካልመጣ ወይም ምንም አይነት የተረጋገጠ PRT PCR ምርመራ ሰርትፊኬት ይዞ ካልመጣ ተለይቶ ወደ ተዘጋጀ ማቆያ ቦታ እንዲገባ ተደርጎ ለ7 ቀናት ክትትል ይደረግለታል፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ወደ ለይቶ ማቆያ የገባ ሰው ናሙና ተወስዶ PRT PCR ምርመራ ከተደረገለት በኋላ ውጤታቸው ኔጌቲቭ ከሆነ አስፈላጊው ምክር ተሰጥቷቸው እስከ 14ኛ ቀን ድረስ በቤቱ ራሱን ለይቶ እንዲቆይ ይደረጋል፤ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤቱ ፖዚቲቭ ከሆነ በተቀመጠው የየኮቪድ-19 የህክምና መመሪያ መሰረት ህክምና እና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፣

## 31.በቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል የኮሮና ቫይረስ PRT PCR ምርመራ ውጤት ሳይዝ የሚመጣ ከስደት ተመላሽን በተመለከተ

1) በቦሌ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ የሚገባ ተመላሾች ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ከሚመጡበት ሐገር ከ72 ሰዓት በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ PRT PCR ምርመራ ሰርትፊኬት ይዞ እንዲመጣ ይደረጋል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ወደ ሀገር የሚመጣ ከስደት ተመላሽ ከ72 ሰዓት በላይ ያልሆነው የተረጋገጠ PRT PCR ምርመራ ሰርትፊኬት ይዞ ካልመጣ፣ተለይቶ ወደ ተዘጋጀ ማቆያ ቦታ እንዲገባ ተደርጎ ለ7 ቀናት ክትትል ይደረግለታል፣

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ወደ ለይቶ ማቆያ የገባ ሰው ናሙና ተወስዶ PRT PCR ምርመራ ከተደረገለት በኋላ ውጤቱ ኔጌቲቭ ከሆነ አስፈላጊው ምክር ተሰጥቶት እስከ 14ኛ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

ቀን ድረስ በቤቱ ራሱን ለይቶ እንዲቆይ ይደረጋል፤ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤቱ ፖዚቲቭ ከሆነ በተቀመጠው የኮቪድ-19 የህክምና መመሪያ መሰረት ህክምና እና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፣

## 32.በቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል የሚያልፍ የትራንዚት መንገደኛን በተመለከተ

1) በቦሌ አለም አቀፍ አየር መንገድ በኩል የሚገባ ማንኛውም የትራንዚት መንገደኛ ወደ አየር መንገዱ ሲገባ ሁለት የአዋቂ እርምጃ አካላዊ ርቀትን የመጠበቅ፤ እጁን የመታጠብ እና የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

2) የኢትዮጵያ አየር መንገድና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የትራንዚት መንገደኛ አየር መንገዱን ለቆ ወደ ከተማ እንዳይገባ ማድረግ ሀላፊነት አለባቸው፤

3) ከ24 ሰዓት በላይ ትራንዚት ላላቸው መንገደኞች በረራቸው እስኪደርስ ለኳራንቲን በተዘጋጁት ሆቴሎች የመቆየት ግዴታ አለባቸው።

## 33. በድንበር በኩል የሚገቡ ሰዎችን በተመለከተት

1) በድንበር በኩል የሚገባ ማንኛውም ሰው የሙቀት መለካትና የኮቪድ-19 ምልክቶች ልየታ ተደርጎለት ተለይቶ ወደ ተዘጋጀ ማቆያ ቦታ እንዲገባ ተደርጎ ለ7 ቀናት ክትትል ይደረግለታል፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ወደ ለይቶ ማቆያ የገባ ሰው ናሙና ተወስዶ ከተቻለ የRT PCR ምርመራ ይደረግለታል፣ ካልተቻለ ደግሞ በምግብና እና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን በተረጋገጠ ፈጣን የአንቲ ቦዲ ምርመራ ስልት (RDT) ይደረግለታል፤

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ወደ ለይቶ ማቆያ የገባ ሰው በ6ኛው ቀን ናሙና ተወስዶ የRT PCR ምርመራ ከተደረገለት በኋላ ውጤቱ ኔጌቲቭ ከሆነ አስፈላጊው ምክር ተሰጥቶት እስከ 14ኛ ቀን ድረስ በቤቱ ራሱን ለይቶ እንዲቆይ ይደረጋል፤ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤቱ ፖዚቲቭ ከሆነ በተቀመጠው የኮቪድ-19 የህክምና መመሪያ መሰረት ህክምና እና ክትትል እንዲያገኝ ይደረጋል፣

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ወደ ለይቶ ማቆያ የገባ ሰው ናሙና ተወስዶ ፈጣን የአንቲ ቦዲ ምርመራ ስልት (RDT) ተደርጎለት ውጤቱ ኔጌቲቭ ከሆነ እና አይጂጂ (IgG)

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

ያለው ከሆነ  አስፈላጊውን ምክር ተሰጥቶት ለተጨማሪ 14 ቀናት በቤቱ ራሱን  ለይቶ እንዲቆይ ይደረጋል፣  አይጂም (IgM) ውጤት ያለው ከሆነ ተጨማሪ የRT PCR ምርመራ ይደረግለታል

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት  በRT PCR ምርመራ ተደርጎለት ፖዘቲቭ ውጤት ያለው  ሰው  በገባበት ድንበር አካባቢ በሚገኝ ለይቶ ህክምና ጣቢያ ህክምና እና ክትትል ይደረግለታል

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 34.የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎችና አሰራሮች

1. የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ መመሪያ ቁጥር 2/2012 አንቀፅ 18 እና 19 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፣
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸዉም ሕጎችና አሰራሮች  በዚህ መመሪያ በተሸፈነ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡

### 35.የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሰዉ ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት መተባበር ግዴታ አለበት

### 36.የህግ ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ ሀላፊነት የተሰጣቸው አካላት፣ ሀላፊነታቸውን ካልተወጡ በአዋጁ መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ

### 37.ማንዋል የማውጣት ስልጣን

የጤና ሚኒስቴር ስለ ግል ህክምና ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ፣ ስለኮቪድ 19 ታካሚዎችና ቤተሰቦቻቸው የምክር አገልግሎት  በለይቶ ማቆያ  የሚደረግ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ ድጋፍአሰጣጥ፣ተጋላጭ ለሆነ የህብረተሰብ ክፍሎች መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄዎችና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ዝርዝር የአሰራር ማንዋል ያወጣል፡፡

## 38. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

1) ይህ የአፈጻጸም መመሪያ በሚኒስትሮች ኮሚቴ ከጸደቀበት ዕለት ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

2) የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተነሳ የዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት አብሮ ያበቃል።

**ሰኔ 11ቀን 2012 ዓ.ም**

**የሚኒስትሮች ኮሚቴ**